**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን**

# ሃያ አምስት ደቂቃ

መጋረጃው እንደ ተገለጠ የግድግዳው አራት ሰአት መሙላቱን አራት ጊዜ በመደወል ያበስራል ፡፡ ቤቱ የሐብታም ሰው ቤት መልክ አለው ፡፡ ፊት ለፊት ወደ ውጪ የሚያስወጣ በር ሲኖር በስተግራ በኩል የመኝታ በሮች አሉ ፡፡ በስተቀኝ ካለው ግድግዳ ላይ አራት ጊዜ የደወለው ትልቅ ሰአትና በስተግራ ደግሞ እድሜያቸው በአርባዎቹ መጨረሻ ላይ የሚገመቱ ሴትዮ ፎቶግራፍ በፍሬም ተሰቅሏል ፡፡ ከግራ በኩል ኮርኒሱ ላይ «መልካም የልደት በአል» የሚል ጽሁፍ በአማርኛና በእንግሊዘኛ ጉልህ ፊደላት ወረቀት ላይ ተጽፎ ተሰቅሏል ፡፡

መሐል ወለል ላይ ትልቅ ጠረጴዛ በሶስት ቄንጤኛ ወንበሮች ተከቦ ይታያል ፡፡ በላዩም ሶስቱ ተለኩሰው ግማሽ የደረሱ የተለያዩ ቀለም ያላቸው ሻማዎችና ከግራ በኩል ደግሞ የተቆራረጠ ቡርቱካኖች ሙዞች የያዘ የሸክላ ሳህን አለ ፡፡ ዘመና አንዳንድ ቁራጭ እያነሳች ወደ አፏ እየከተተች የስጦታ ካርዶችን ታያለች ከአጠገቧ አቶ አጥናፉ ነጭ መነጽራቸውን እንደሰኩ በወፍራም የሌሊት ልብሳቸው ላይ ጋቢ እንደደረቡ እያፋሸኩ ወረቀቶች ያጋላብጣሉ ፊት ለፊታቸው ረጅምና ጥቁር ቦርሳቸው አለ ፡፡ ሰአት ካለበት ግድግዳ ስር ካለ ወንበር ላይ እማሆይ ሀና ተቀምጠው ከመቁጠሪያቸው ጋር ያወጋሉ፡፡ በተቃራኒው አቅጣጫ ደግሞ ዘውዱ ተቀምጦ የቪዲዮ ፊልም ካሴቶችን ያገላብጣል ፡፡

ከጥቂት ቆይታ ቡሃላ ዘመናይ ካርዶቹን ሰብስባ ዓይኗቹን እያሻሸች በስተቀኝ በኩል ጓዳ ትገባለች ፡፡ ወዲያው ዘውዱ ካሴቶቹን ይዞ እማሆይንና አባቱን ተመልክቶ እንደገና የእጅ ሰአቱን በመገረም ያይና ዘመናይ በገባችበት ይገባል ፡፡ ከጥቂት ፋታ ቡኃላ ደግሞ እማሆይ ፀሎታቸውን ጨርሰው በስተቀኝ በኩል ካለው ጓዳ ይገባሉ በመጨረሻም አቶ አጥናፉ ተንጠራርተው ቤቱን አስተውለው ወረቀቶቻቸውን በቦርሳቸው ከተው ሻማዎቹን ያጠፋሉ ፡፡ ሙሉ ጨለማ ፡፡ ጥቂት ቆይቶ ሙሉ ብርሀን ይበራል ፡፡ በመጀመሪያ አቶ አጥናፉ ቀጥሎ ዘመናይ

አቶ አጥናፉ ፡- /ቁና ቁና እየተነፈሱ / አቤት! አቤት ! . . . አቤት ጥቁረት ፡፡

እማሆይ ፡- /እየተንቀጠቀጡ / እግዚኦ ! እግዚኦ ! መሀረነ ክርስቶስ ልጅ አጥናፉ ምን ጉድ መጣብን

ዘውዱ ፡- /እየተጠጋቸው / አባዬ አንተም ጋር መጥቷል እንዴ ? . . . እማሆይ ለእርስዎም ተገለጸሎት ? ዘመናይስ እንዴት ከእንቅልፍሽ ተነሳሽ ?

ዘመናይ ፡- /እየተንቀጠቀጠች/ በስመ አብ . .. በስመአብ . ... .እንዴት ያስፈራል . . እኔም አይቼዋለሁ . . . አቤት ቀመቱ . . . ./ፋታ/ ግን ምን ታያላችሁ ?

አቶ አጥናፉ ፡- በእያንዳንዳችን አልጋ መጥቷል ማለት ነው ? ምኑን ነው ያየሽው ልጄ ? የዛሬ ቀን ለኛ አልበጀንም ምን አይታችኋል እናንተ ?

እማሆይ ፡- (ራሳቸውን ይዘው) ኧረ እንዴት ይዘገንናል ! እግዚኦ ክርስቶስ!

ዘውዱ ፡- ግን ምንድ ነው እሱ ? እውነት እኔ እንዳየሁት እናንተም አይታችሁታል ?

አቶ አጥናፉ ፡- ምን ይላል ይሄ ! ታዲያ ከተኛንበት ምን እያበረረ ደም እንዳስከረው አክለፍልፎ አስወጣን፡፡

ዘመናይ ፡- እኔ በደንብ አይቼዋለሁ-ቀመቱ እንደ ረጅም ዛፍ ያክላል-በቀኝ እጁ የእሳት ሰይፍ ይዟል ፡፡ ዓይኖቹ ውስጥ እሳት ይነዳል ፡፡ ጥርሶቹ ደግሞ.....

ዘውዱ ፡- /አቋርጧት / በቃሽ ! እሱ ነው ለኔም የታየኝ ፡፡ በዚህ ምድር ላይ አያሌ ተአምራቶች እለት ከእለት ይከሰታሉ- ዛሬ በዚህ ቤትም ይሔው ተከስቷል ሁላችንም ካየነው ያየነው ሰይጣን ነው

አቶ አጥናፉ ፡- ኧረ ምን ይሻላል እማሆይ ሐና ? ቅዠት ነው እንዳልል ሁላችንም ልንቃዠ አንችልም

እማሆይ ፡- ቀጣ ነው የኃጢያታችን ብዛት ነው ፡፡ /ይንበረከካሉ / እግዚኦ ! እግዚኦ መድኃኒዓለም !

ዘውዱ ፡- እንዴት ይታመናል አሁን ይህንን ሰይጣን ሁላችንም አይተነዋል ?

እማሆይ ፡- ሰይጣን አይደለም ልጄ ፡፡ እኔ በደንብ አውቀዋለሁ ፡፡

ዘመናይ ፡- ታዲያ ምንድ ነው እማሆይ

እማሆይ ፡- መልአከ-ሞት ነው፡፡

ሁሉም /በከባድ ድንጋጤ በአንድነት /መልአከ ሞት!!!??? (በፍጥነት ዘውዱ ከጠረጴዛው ስር ሲደበቅ ዘመናይና አቶ አጥናፉ በየመኝታ ክፍላቸው ይገባሉ)

እማሆይ ፡- /ከተንበረከኩበት በድጋጤ ተነስተው / ልጅ አጥናፉ ልጅ አጥናፉ ፡፡ ኧረ አንተ እንኳ ውጣ  ልጅ አጥናፉ ! /ፋታ/ ዘውዱ ! ዘውዱ !

ዘውዱ ፡- /አንገቱን ብቻ ብቅ አድርጎ/ እማሆይ አትድከሙ አባዬ ሲፈራ እኔ የምደፍር ይመስልዎታል

አቶ አጥናፉ ፡- /ከጓዳ ሆነው / ዘመናይ ! ዘመናይ !

ዘመናይ ፡- /ከገባችበት ሆና / አባዬ ኧረ እባክ ውጣ ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- /ሹክክ ብለው ይወጣሉ / እግዚአብሔር ዛሬ በኛ ፈርዷል ማለት ነው ፡፡ ለዚህ ነው መልአከ ሞትን ወደኛ የላከው ፡

ዘውዱ ፡- /ከተደበቀበት እየወጣ / ትሰማላችሁ ይሰማችኋል  ከሰላሳ ደቂቃ ቡኃላ ተመልሼ

እመጣለሁ ብሏል እኮ ፡፡ ሞት ደፍሮ መጣሁ ሲል ማን ደፍሮ እጅ ነስቶ ይቀበለዋል ፡፡

ዘመናይ ፡- እንጃ ግን እንደሚመጣ ሲናገር እኔም ሰምቻለሁ ፡፡

እማሆይ ፡- እውነት ነው የቤታችን የኃጢአት ገንዳ ስለሞላ እግዚአብሔርን የቁጣ በትሩን አነሳ

አቶ አጥናፉ ፡- ሽብር የለቀቀብኝ'ኮ መልአከ-ሞት በዛሬው ሌሊት አንዳችንን ለመውሰድ እመለሳለሁ ማለቱ ነው ፡፡

ዘመናይ ፡- ምን እሱ ብቻ ከመካከላችሁ አንድ ሰው ካልመረጣችሁና ሰዓቱ ከደረሰ ሁላችንም በመብረቅ አጠፋለሁ ብሏል ፡፡

ዘውዱ ፡- ምን ማድረግ እንዳለብን በእርግጥ አላውቅም፡፡ ማንስ ቢሆን ምን ማድረግ ይችላል? ሞት መኖሩን እንደ ጥላም ሥር ስራችንን እንደሚከተለን ማንም ያውቃል ፤ ግን ደግሞ ግን ደግሞ ይረሳል ፡፡ እንዲህ ብቅ ሲል ደግሞ ጭንቅ ነው ፡፡

እማሆይ ፡- እባካችሁ ተንበርከኩና ፀልዩ ምናልባት ፀሎታችንን ሰምቶ እግዚአብሔር ይምረን ይሆናል

ዘውዱ ፡- ወይ ፀሎት! የግድግዳውን ሰዓት ትመለከታላችሁ ፣ ለስድስት ሰአት ሃያ አምስት ደቂቃ ብቻ ነው የቀረው ስድስት ሰአት ሲሆን ተመልሶ ይመጣል

ዘመናይ ፡- እና ሰዓቱን እንጠቀምበታ ! እጅና እግራችንን አጥፈን ሞት አንስቶ ይውሰደን ወይኔ ! . . . . .ወይኔ ! /ራሷን በእጇቿ ትይዛለች /

ዘውዱ ፡- እኔ እንዲህ ዓይነት ነገር ከተፈጠርኩ ጀምሮ ሰምቼም አይቼም አላውቅም ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- ከዛሬ በቀር እኛም አይተን ፣ ሰምተን አናውቅም

ዘመናይ ፡- ከሞት ጋር እኮ ነው ቀጠሮ የያዝነው ፡፡/ፋታ/ አንድ ሃሳብ አለኝ ፡፡ ለምን ቤቱን ጥለን አንጠፋም

አቶ አጥናፉ ፡- አትድከሚ ልጄ ! መልአከ ሞት ከአይኔ የሚሰወር አንዳች የለም ፡፡ ወዴትም ለመንቀሳቀስ እንዳትሞክሩ . . . . አላላችሁም ?

እማሆይ ፡- አዎ ! አዎ ይላል ብሏል ! ደግሞስ ሸሽተን የት እንደርሳለን ?

ዘመናይ ፡- እና ታድያ የማታውን ፌሽታና ደስታችንን በጥሩ እንቅልፍ ሳናጣጥመው ከመካከላችን አንዱ በሞት ይነጠቅ ? እስኪ አስቡት መልአከ ሞት ከጥቂት ደቂቃ ቡኋላ መጥቶ በዚያ ጅማታምና ረጃጅም እጆች ጉሮሮአችንን አንቆ ነፍስና ስጋችንን ሲለያየው ይታያችሁ ፡፡

ዘውዱ ፡- እሺ አየነው ዘመናይ በደንብ እየው ይሄ እንዳይሆን ግን ምን እናድርግ ?

ዘመናይ ፡- ከሁለት ሰዓታት በፊት እኮ ባመጣሁት ጥሩ የማትሪክ ውጤትና ልደቴንም አስበን ሁላችን ፈንጥዘን የደስታ ቀን አዘጋጅተን ነበር ፡፡ ከወዳጅ ዘመዶቻችን ጋር ተሳስበን ስንጨፍር ነበር'ኮ

እማሆይ ፡- እውነት ነው የቤታችን ኃጢአት ገንዳ ስለሞላ እግዚአብሔር የቁጣ በትሩን አነሳ ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- ምን ዋጋ አለው ፡፡

ዘውዱ፡- ለካ ደስታ ጤና ናት የሚባለው እውነት ነው ፡፡ /ይስቃል /

ዘመናይ ፡- ምን ያስቅሃል

ዘውዱ ;- አማራጭ አጣን ፡፡ በማታው የአለም ዘጠኝ ፌሽታ ልደትሽና ለውጤት መብቃትሽ ገጥመው ለድርብ ደስታሽ ተርታ ሰርተን « ሀፒ በርዝ ዴ ቱ ዩ እያልን ዘምረን ነበር ፡፡ አሁን ደግሞ ተገለባብጧል ሳት ወደ ለቅሶ ደስታ ወደ ሀዘን ተለውጧል ፡፡ በዚህ ሰአት ከመጮህ አልያም ከመሳቅ ውጪ ምን ማድረግ ይችላል

እማሆ ፡- እውነት ብልሃል ዘውዱ ደስታ ጤዛ ናት ደስታ ሲበዛ ደግ አይደለም ያልኩትን አልሰማችሁም ነበር ፡፡ ካለመጠን ትጮሁ ነበረ ጩኸታችሁን እግዚአብሔር አልወደደውም ፡፡

ዘውዱ ፡- ይህ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ ልብ ይሉ እንደ ሆነ የዛሬ ሶስት ዓመት ገደማ እማዬ በመኪና አደጋ የእርሶ ባለቤት ደግሞ ያልታወቀ ጠላት በሚጠጡት ጠላ ላይ መርዝ ጨምሮ ሳይገድላቸው ጩኸት ጭፈራ ነበር? ታዲያ. . . .

እማሆይ፡- /እንደ መወራጨት ብለው / እባክህ ልጄ መንፈሴን አታቫክረው፡ ፡የባለቤቴን ነገር አታንሳ /ራሳቸውን በእጃቸው ይይዛሉ/ አታንሳው! . . . .አታንሳው!

አቶ አጥናፉ ፡- እዉነታቸውን ነው! ጠላታችንን እስከ ዛሬ ሳናውቀው ፣ ደሙን ሳንመልስ በሜዳ ቀርቶ ለምን አሁን ታነሳዋለህ?

ዘውዱ ፡- /ለማስረዳት እየጣረ / ማለቴ'ኮ እሳቸው በዚህ ሰበብ ከመመንኮሳቸው በፊት በቤታችን ብዙ የደስታ ምሽቶች እናሳልፍ ነበር ለማለት ነው ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- ደስታችን እኮ ሀዘን ጠራብን

ዘመናይ ፡- ለዚህ ምን ማስረጃ ያሻል ከሰአታት ቡኃላ የነበረውን ካስታወስን ይበቃል ፡፡ ከሰአታት በፊት በብዙ ደስታ ደምቆ የነበረው ሳሎን አሁን እንደ በረዶ ቀዝቅዞ እኛም ከሞት ጋር ቀጠሮ ይዘናል /ሁሉም ቁጭ ብለው ይተክዛሉ)

ዘውዱ ፡- ግን እኮ ላይመጣ ይችላል ፡፡ ምናልባት።

አቶ አጥናፉ ፡- እንደማይቀርማ በጥብቅ ነግሮኛል በተናገረ ቁጥር የተቆራረጠ እሳቶች ከአፉ እየወጡ ከመካከላቸው አንድ ሰው መርጣችሁ ጠብቁኝ ነው ያለኝ

እማሆይ ፡- እግዚአብሔር አዞት ስለሚመጣ በጭራሽ ሊቀር አይችልም

ዘውዱ ፡- ወይ ደግሞ ቤት ተሳስቶ ሊዘለን ይችላል

ዘመናይ ፡- ግን ሕይወት ምንድናት የምንኖረው ከንቱ ነው ማለት ነው ድካማችንና ሩጫችን ሁሉ እንዲህ በከንቱ ለመቀጨት

ዘውዱ ፡- የመጨረሻው የሰው ልጆች አስቀያሚ ዕጣችን ታዲያ ምን ሆነና? ለትንሽ ለትልቁ ተንገብግበን ቀድመን ለማለፍ አንዱን ጥለን በአንዱ ትከሻ ላይ አንዳችን ቆመን

ዘላለም ተተክለን የምንኖር ይመስል መባላታችን እኮ ነው የሚገርመው ደግሞም በማንኛውም ሰአት መቃብር ለመውረድ

አቶ አጥናፉ ፡ መቼ ይሄንን እናስባዋለን ታዲያ ፡፡ /ይነሳሉ / ወይኔ አጥናፉ ! ገንዘቤን ሁሉ አበድሬ አበድሬ ልከስር

ዘመናይ ፡- አባዬ አሁን ስለገንዘብ የምታስብበት ሰአት ነው /ፋታ/ እኔ በፍጹም መሞት አልሻም እሺ የጨብጥነው ምርኩዝ ሲሰበር ተስፋችንን ሁሉ ጨለማ ሲያጠቁረው ቅድም የነበረው አሁን ደብዛው ጠፍቶ ፣ እንዲህ ሲሆን ምን ይባላል

ዘውዱ ፡- ምንም ምንም አይባልም ቅድም ሌላ አሁን ሌላ ቅድም ላንቺ ደስታ ሻማዎች በረድፍ ተለኩሰው ዳቦ ቆርሰን ነበረ ፡፡

ዘመናይ ፡- ግን ያ ሁሉ እንደ ጠዋት ጤዛ ረግፎ በምትኩ ሞትና ጨለማ ከቦናል ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- አይ የቀን ጎደሎ አይ የቀን ፍርጃ /በጭንቀት ይንቆራጠጣሉ /

ዘውድ፡- ምነው ገና ቀን ወዲህ ሲመጣ እግሬን በሰበረው ነበር ፡፡ ያንን የመሰለ ጨዋታ አቋርጬ ጓደኞቼን አስቀይሜ በመምጣቴ ነው ይሄ መዘዘኛ ፓርቲ ምነው። የማትሪክ ውጤትሽ በሙሉ ኤፍ በሆነ ነበር ፡፡

ዘመናይ ፡- /በንዴት / ለምን አንተ ! የኔ ውጤት ማምጣት ነው እንዴ ሞት ያመጣብህ

ዘውዱ ፡- አንቺ ይሄንን ፓርቲ ባታዘጋጅና ዛሬ እንድመጣ ባትወሰውሽኝ ኖሮ ይሄኔ እዚህ ቤት እመጣ ነበር ፡፡ ከዚያች ነጭናጭ ቤት አከራዬ አሮጊት ጋር በሙብራቱ በውሃው ስከራከር አመሽ ነበር

አቶ አጥናፉ ፡- /በቁጣ/ ዝም በሉ ወዲያ ልክፍተኞች

አማሆይ፡- የትም ቢሆን የትም እግዚአብሔር ያዘዘው አይቀርም እኮ ልጄ እኔንስ በምክንያቱ ከገዳሙ ጠርቶ እዚህ ያቆየኝ በጥበቡ አይደል ፡፡ ደግሞስ እመመኔቷ እስከ ዛሬ ለስራ እያሉ የሚልኩት ሌላ ሰው አልነበር ቢያዝብኝ ነው እንጅ

ዘውዱ ፡እግዚአብሔር ቢሆን ካላጣው ቀን ሞትን ያክል ጠላት ዛሬ ይልክብናል? አሁን የሚሞት ሌላ ሰው አዋሳ ውስጥ አጣና ነው? ከምንም በላይ ደግሞ የሚያበሽቀው ይሄ ነው

አቶ አጥናፉ ፡- አዬ መከራዬ እንዴት ያለው ኃጢአት ቢኖርብኝ ነው?

እማሆይ ፡- አራጣው ነው፡፡ ያፈሰስከው የሕዝብ እንባ መና ይቀር ይመስልህ ነበር? አራጣ ስታበድር ወልደህ ስመሃል ፣ ዘርተህ ቅመሃል ፤ ወደ ፈጣሪ ፊትህን አዙር ብልህ፤ በአባቶችም ባስመከርህ አሻፈረኝ ብለህ ፀናህ ፡፡ ባናት ባናታቸው ወለድ አየጫንክ ስንቱን መና አስቀረህ ይሄስ ሌላ አያመጣም ፡፡

አቶ አጥናፉ፡- እና ታዲያ አልቀማሁ፡፡ ተቸገርኩ ብሎ እግሬ ሥር ወድቆ ሲለምነኝ ሁሉ ሰጠሁ ፡፡ በችግሩ ደረስኩለት ሁሉም ወዶ ይወስዳል እና የኔ ኃጢአት እምኑ ላይ ነው ?

እማሆይ ፡- ወለድ ማበደርህ ኃጢአቱማ ያንተ ያልሆነውን እየደረብክ መውሰድህ የወ/ሮ ላቀችን ቤት አላሸጥክም? የአቶ ክብረትን መኪና ወርሰህ ለልጅህ መስጠትህን ትረሳለህ ?

ዘውዱ ፡- አ!አ ! . . . . ወደ ታከስዬ እንኳን ማንም መምጣት አይችልም እማሆይ ሹፌር ቀጥሬ ራሴን ችዬ ጌታ ሆኜ የምኖረው በሷ ነው ፡፡

ዘመናይ፡- /በንዴት / አሁን ይሄንን ሁሉ መዘርዘር የሚረባን ነገር አለ ? በጣርና በሞት አፋፍ ሆነን ይሄንን መነጋገር ይገባናል ፡፡

እማሆይ ፡- አዎ እግዚአብሔር ይሄን ዓይነቱን ቁጣ እንደምን ላከብን ብሎ መመራመር ያሻል በደልን አውቆ ምህረትን መለመን ከተሻለ ሰይፍ ያድናል ፡

አቶ አጥናፉ ፡- እንዴ ! መልአክ ሞትን የሚልከው እራሱ እግዜሩ ነው አላሉም አሁን? እማሆይ መልሰን ደግሞ እሱኑ እንለምነው

እማሆይ ፡- አዎ ! እግዚአብሔር ትግስቱ ብዙ ነው ፡፡ ምህረቱ ወሰን የለውምና እንለምነው፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- እሄሄ. . . . ስንት ዘመን ሌሊቱን እየወሰደ ቀኑን ቀኑን እየወሰደ ሌሊቱን ሲያፈራርቅ ተመስገን ያላልኩት አምላክ ዛሬ ሰማኝ ብለው እሺ ይላል?

ዘውዱ ፡- እኔ ግን የሚሰማን አይመስለኝም ፡፡

ዘመናይ ፡- ለምንድን ነው የማይመሰልህ? ከእማሆይ መፍትሔ ውጪ አማራጭ የለም

እማሆይ ፡- ሳትራመድ ደከምክ እኮ ልጄ ለምን አይሆንም አይሰማንም ትላለህ ?

ዘውዱ ፡- «ሳይያዙ ነው ሳይያዙ ፤ ከተያያዙ ብዙ ነው መዘዙ ይባላል እኮ ፡፡ከተያዙ ወዲ መንፈራገጥ ለመጋጋጥ ነው፡፡ ፍርዱ አንዴ ከላይ ፀድቆ ፋይላችን ከወረደ ወዲያ ብንጮህ ማን ይሰማናል፡፡

እማሆይ፡- እግዚአብሔር እራሱ ይሰማናል ፡፡

ዘውዱ ፡- ኋላ ግን ውሳኔዬን ለመሻር አሲራችኋል ብሎ ደቂቃዎቹን እንዳያሳጥራቸው /ወደ ሰዓቱ አይቶ) በጣም ይጮሃል፡፡ በአንድነት ዝም ያሰኙታል

አቶ አጥናፉ ፡- ኧረ እባክህ ዝም በል አንተ ሰይጣን

ዘውዱ ፡- ምኑን ዝም አላለሁ አስራ ስምንት ደቂቃ ብቻ ነው እኮ የቀረን

እማሆይ ፡- እባክህ ልጅ አጥናፉ . . .ዘውዱ እባክህ ፈጣሪን እንማጠን . . . በሞተች እናትህ..በጡሪዬ ይሁንህ ፡፡

ዘውዱ ፡-ደህና! ደህና! ተስፋ ከመቁረጥ በተስፋ መራመድ የተሻለ ነው፡፡ /ሁሉም ተያይተው ይንበረከካሉ / ተስፋ ትልቅና ጣፋጭ የመንፈስ ኬክ ነው፡ ወይም ደግሞ ነው ይባላል በዚህ ግን ማናችንም ራሳችንን መሸንገል የለብንም "በተስፋ የሚኖር በርሀብ ይሞታል » አንዱ ደራሲ ተስፋ . . . .

ዘመናይ ፡- በመሰልቸት ምናለ መለፍለፍከን ብታቆም ዘውዱ ፡፡ በፀሎት ሰዓት ፍጹም ፀጥታ ያሻል ሁላችንም በየልባችን እንፀልይ ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- ኧረ እባክሽ አንቺ ልጅ በየልባችን አይሰራም በአንድነት ነው፡፡ /ፋታ/ እኔ የምለውን እየተቀበላችሁ ትላላችሁ ፡፡ /ፋታ/ አይናችሁንም፡ እጃችሁንም አንሱ...ወደ ላይ አንሱ! (ሁሉም ያነሳሉ አቶ አጥናፉ ጉሮሮአቸውን ጠራርገው) እግዚአብሔር ሆይ . . ./ ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው / በለሆሳስ በሉ . . . እግዚአብሔር ሆይ . . .

እማሆይ ፡- (አቋርጠው) በስመአብ ብለህ ጀምር እንጅ ልጅ አጥናፉ ፡፡

ዘውዱ ፡- እንዲያ ከሆነማ ፀሎቱ መርዘሙ ነው ፡፡ ከሰዓት ጋር መብረር አለበት እማሆይ

አቶ አጥናፉ፡- /በንዴት / መልአከ ገብርኤል ክንፍህን ያብረው! ምናለ የሚደረገውን ብታደርግ ሰው እድሜውን በቧልት ይጨርሳል /ፋታ / በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን !! በአንድነት አሜን ይላሉ / እግዚአብሔር ሆይ እንደምንወድህ አንተ ታውቃለህ እንደምናከብርህ አንተ ታውቃለህ እንደምፈራህ አንተ ታውቃለህ አዎን እግዚአብሔር ሆይ እርግጥ ነው እንወድሃለን እግዚአብሔር ሆይ እናከብርሃለን፡፡ እግዚአብሔር ሆይ እንፈራሃለን፡፡ እግዚአብሔር ሆይ....

ዘውዱ ፡- (አቋርጧቸው) ይሄ እኮ ምን አይሰራም አባበ? ትርፉ ሰዓት መግደል ነው። መልአከ ሞትን መልሰው ወይም ወደ ሌላ ላከው ማለት ነው ደጉ፡፡

ዘመናይ ፡- በተጨማሪም አባዬ እግዚአብሔር መነጣጠልን ፤መለያየትን ፤ አይወድምና እንዳይነጣጥለን ለምነው፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- ጥሩ ጥሩ . . .አዎ እግዚአብሔር ሆይ ልጄ ዘመናይ እንዳለችው እኛ በጣም እንፈቃቀራለን መለያየት በፍጹም አንሻም፡፡ እግዚአብሔር ሆይ ፍቅራችንን ጹኑ መሆኑን ታውቃለህና አንዳችን ከአንዳችን ተነጣጥለን መኖር አንችልምና አትለየን

እማሆይ - የተሰወረና ለአንተ ግን የተገለጠ ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር በለን በደላችንን ሁሉ ደምስስልን እንበል እንጂ...

አቶ አጥናፉ ፡- ጥሩ ጥሩ . . . . ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር በለን ፡፡

እማሆይ ፡- አራጣ በማበደር ያልሰራሁትን እየቀማሁ የኖርኩበትን ዘመንን ይቅር በለኝ በለው

አቶ አጥናፉ ፡- ምን ይህ ደግሞ ከዚህ ጋር ምን አዛመደው እማሆይ ይሄን ካልኩ እኮ ሁለተኛ አላበድርም በክስና በክርክር ላይ ያሉትን በሙሉ እተዋቸዋለሁ ማለት ነው ፡፡

ዘውዱ ፡- መሆኑ ነው አባባ?

እማሆይ ፡- እንግዲያስ

አቶ አጥናፉ ፡- በጭራሽ! በጭራሽ አላደርገውም /በእህልና ቁጣ/ አሁን የአቶ በቀለን ጉዳይ እንድተወው ማለት አርባ ሺ ብሬን ልጦ የለኝም እኮ እያለ የሚያጭበረብረው ያንን መልቲ ልምረው አላደርገውም ፡፡ ሕግ ፊት አቀርበዋለሁ በቅርቡ ከነወለዱ ስልሳ ሺ ብሬን ይተፋታል ፡፡

ዘውዱ ፡- /እየተሰና / በቃ! በቃ! . . .እዚህ ላይ በርሱ ነገር ፋርሽ ሆኗል፡፡ ፀሎታችንን ውድቅ ሆኗል፡፡

እማሆይ ፡- ኧረ እባካችሁ ልብ ይኑራችሁ "ቂም ይዞ ፀሎት ሳል ይዞ ስርቆት" ይባላል ከነተረቱ ምነው በንፁህ ልብ ብንለምነውና . . . . .

አቶ አጥናፉ ፡- /እየተነሱ እሄሄ. . . እናንተማ የት አይታችሁ ይሄ መናኛ መልቲ እንዲያ እግሬ ስር ተንበርክኮ እንባውን እየዘራ እንዳልለመነና እንዳልተበደረ ዛሬ ኩታውን አፍንጫው ድረስ ተከናንቦ ገንዘብህን ለመስጠት አልችልም ፡፡ከሰሰኝ ይለኛል!?

ዘመናይ ፡- ደቂቃዎች እየበረሩ መሆኑን ዘንግታችኋል ልበል ? /ትነሳለች/ ፀሎቱን ከተዋችሁ ሌላ ፈጣን አማራጭ መፈለግ አለባችሁ

ዘውዱ ፡- /ጠረጴዛው ላይ ካለው የሸክላ ሣህን ላይ የሙዝ ቁራጭ አንስቶ በልቶ «ወይ ጉድ !ምን እግር ጣለኝ አለ ፈረንጅ ጣሊያን" ሰክለፈለፍ መጥቼ ሞት፡፡ ኧረ እናንተ ሰዎች እባካችሁ በፀሎታችሁ እርዱኝ ፡፡ ፀሎታችንን እንቀጥል ፡፡

እማሆይ ፡- /ተስፋ ቆርጠው እየተሰኑ / እንግዲህ ከዚህ የተሸለ ምን ሊመጣ እግዚአብሔር ያመጣውን የሚመልሰው እሱ ብቻ ነው ፡፡ ይህም የሚሆነው በፀሎት ነው ፡፡ የነነዌን ከተማ አታስታውስም የነነዌ ሕዝብ . . . .

ዘውዱ ፡- /አቋርጧቸው / እማሆይ ይተውት ታሪኩን ከጀመሩት ለመጨረስ የሚያበቃን ጊዜ የለንም ፡፡

እማሆይ ፡- እሱ ፈጣሪ ያዘዘውን ማን ይሽረዋል ? እንግዲህ

አቶ አጥናፉ ፡- ከዚህ የተሻለ ሌላ መላ ይፈለግ ፡፡ ልጆቼ ፊደል ከቆጠረ ብልሃት አይጠፋምና መላ አምጡ፡፡

ዘመናይ ፡- እኔ ኡ!ኡ!. . .እሪ ብዬ መጮህ ነው ፡፡

ዘውዱ፡- /ስቀባት / ምስኪን ! ማንም አይደርስልሽም ፡፡ ላንቃሽ እስኪተረተር ምላስሽ እስኪሰነጠቅ ድረስ ብትጮሂ ማንም በዚህ ውድቀት ዘር አይልም ፡፡ ደግሞሞ ከባድ ብርድ አለ፡፡

እማሆይ ፡- አታስቢው ልጄ መልአከ ሞት ሰዎች ከመድረሳቸው በፊት አንቆ ይገድልሻል እና ጩኸቱ ይቅርብሽ ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- እና ታዲያ ምን ይደረግ ? መልአከ ሞት እኮ ወደዚህ እየገሠገሠ ነው ፡፤

ዘመናይ ፡- ከመካከላችን አንዱ ፀሐይን ዳግም የማየት እድል ከእንግዲህ አይኖረውም ብርሃን ለዘላላም አያገኝም ፡፡

ዘውዱ ፡- ለመሆኑ ግን ይህ መልአከ ሞት የወሰደውን ነፍስ የት ያደርገዋል ?

እማሆይ ፡- እንደ የስራችን ሚዛን ከደፉን ገነት ከሚዛን ከጎደልን ሲኦል ፡፡

ዘመናይ ፡- /ዝግንን እያላት / ሲኦል . . .ውይ . . . ከእኛ ወስጥ ማንም ሲኦል መግባት የለበትም ፡፡

ዘውዱ ፡- ማንም ሰው ዳግም ገነት የመግባት እጣ የለውም ?

ዘመናይ ፡- ለምን የለውም ? ሲኦል እኮ ጨለማ ዓለም ነው፡፡ ሲኦል እኮ ጨለማ ባሕር ውስጥ መጣል ነው ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- ቄሶቹ እንደሚሉትማ እስከ ፍጻሜው ከጨለማ አይወጣም ፡፡ኧረ እንዴት ያስፈራል፡፡

ዘውዱ ፡- እሱ ውስጥ ላለመግባት ደግሞ እያንዳንዱን ሰው ቢያንስ የበጎ መንፈስ ባለቤት መሆን እንዳለበት በልጅነታችን ተምረናል ወይም ደግሞ ሰምተናል ፡፡ ከገነት ለመግባት ውድድር ውስጥ የሚገባ እንኳን ቢገኝ ራስ ወዳድ መሆን የለበትም ነፍስ ገዳይ መሆን የለበትም . . .እ. . .ቀናተኝነት ፣ተንኮለኝነት ፤ኧረ ስንት ነገር አለ

እማሆይ ፡- ታድያ ይሄንን ማን ያውቀዋል? ማለቴ . . .

ዘውዱ ፡- /አቋርጧቸው / እያንዳንዱ ሰው እኔ ማን ነኝ እያለ እራሱን መጠየቅ ይገባዋል እስኪ ለአፍታ ከራሳችን ጋር እናውራ፡፡ አሁን ከእኛ ውስጥ ለገነት የሚያበቃው ስራ ያለው አለ?

አቶ አጥናፉ ፡- «ጽድቁ ቀርቶብኝ በወጉ በኮነነኝ » አለ ገብሬ ቶፋው ፡፡

ዘመናይ ፡- እና ወደ እሳቱ ልንሄድ ?

ዘውዱ ፡- መመዘኛውን ካላሟላንማ ግድ ነው ፡፡ አራጣ ማበደር ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ወንጀል ነው ፡፡ ጫት መቃም ሲጋራም ቦታ የለውም ፡፡ ለምድራዊ ትምህርትና እውቀት ብቻም መሮጥ ትርጉም የለውም ፡፡ ምናልባት ግን እማሆይ . . . .

እማሆይ ፡- /አቋርጠውት / እኔስ ብሆን ምን ምግባር አለኝ ፡፡ ስውር ኃጢያቴን እኔ እንጅ ማን ያውቀዋል ? መቼ ፍሬ አፈራውና ልጄ ፡፡

ዘውዱ ፡- ይህ ከሆነ ሁላችንም በሲኦል ነዳድ ለመለብለብ ነው የምንሄደው

ዘመናይ ፡- እኔ በፍጹም አልሄድም በፍጹም

አቶ አጥናፉ ፡- እህ እኛ ሐኪም አዞልናል እንዴ ? ማን ወዶ ይሄዳል ልጄ

ዘውዱ ፡- ግን ከመካከላችን አንዱ ሊሄድ ግድ ነው

እማሆይ ፡- የማይጣስ ትዕዛዝ ከሰማይ ወርዷል ፡፡ ተንበርክከን በእንባችን ጭመር ካልተማፀነው በቀረ ዛሬ መዳኛ የለንም ፡፡

ዘውዱ ፡- ፀሎቱማ በፍጹም አይሠራም መጮህማ አላዋጣም ፡፡

ዘመናይ ፡- መሬትስ ቆፍረን ብንደበቅስ

ዘውዱ ፡አንድ ጉድጓድ ምሰሽ ሳታጋምሺ ሰዓቱ ይሞላል ፡፡ በሰዓቱ የሚፈለገው ሰው ካልተመረጠ ደግሞ እቶን እሳቱ በቤታችን ላይ ይወርዳል ፡፡እናም ሁላችንም እናልቃለን ፡፡

ዘመናይ ፡- ግን አባዬ መልአክ ሞት ጥይት አይፈራም ?

አቶ አጥናፉ ፡- እኔ ምን አውቄ ልጄ ፡፡

እማሆይ ፡- አይፈራም! ፈጽሞ አይፈራም፡፡ ዲሞትፈር ቢይዝ ፣ ምንሽር አልቤን ቢታጠቅ ፣ናሲማስር እሱ እንደሁ ዋዛ . . . . . .መድፍ የጨበጠውንም ቢሆን ከታዘዘ ይዞት ሹልክ ይላል ፡፡

ዘውዱ፡- እሺ አንዴ የመጨረሻ ሙከራ እናድርግ ፡፡ ለሁለት ደቂቃ ብቻ በፀጥታ ሆናችሁ እንዴት ማምለጥ እንደሚቻል አሰላስሉ ፡፡/ሁሉም ያስባሉ ዘውዱ ከብርቱካኑ ቁራጭ እንዷን አንስቶ ይበላል /

ዘመናይ ፡- አሁን አንድ ግሩም ሀሳብ መጣልኝ /ሁሉም አፍጥጠው ያዩታል/ እየውላችሁ ልክ መልአክ ሞት እየበረረ እንደመጣ ሁላችንም እጃችንን ወደ ላይ ከፍ አድርገን እግዚኦ ማረን . . .እያልን እንጮሃለን ደንግጦ እንደቆመ በጣም እያስተዛዘንን እንለምነዋለን

ዘውዱ ፡- በጣም ስቆ/ አየ ልመና! ዘመናይ መልአክ ሞት እኮ አንድና አንድ ስንት ነው ብትይው የማይመልስ ልመና ብሎ ነገረ በጭራሽ የማይገባው ነው ፡፡

ዘመናይ ፡- /በጣም ፈርታ / ኧረ እባክህ ዝም በል ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- /በቁጣ ነደው / ዕድሜያችንን የባሰ ልታሳጥረው ተነስተሃል እንዴ አንተ ከይሲ ይሄ ሁሉ ድንፋታስ የት ለመግባት ነው፡፡ . . .ዋ ! ይሰማህና

ዘውዱ ፡- ታዲያ ፈርተን የምናመጣው ለውጥ ከሌለ ተሸማቀን እንሙት እንዴ ?

እማሆይ ፡- ልጆቼ የሚያስፈራው እኮ ሞቱ አይደለም፡፡ ከሞትማ ማን ይቀራል ? ማንስ ተሸሽጎ ያመልጣል ?

አቶ አጥናፉ ፡- እንዴ . . . . ታዲያ ማንን ፈርተን ጭብጥ ስንዴ አክልን እማሆይ ሞትንማ ነው የፈራነው በዚች ምድር እንደዋተትን ያሰብነው ሳይሞላ ፣የዘራነው ሁሉ ሳናጭድ እንዲህ አይነቱን መቅሰፍት ሲላክብን ሞትን ያክል ባላጋራ አፍጦ ሲመጣብን እሱን መፍራት የት ይቀራል ፡፡

ዘመናይ ፡- ኧረ ያስፈራል ፡፡ በጣም ያስፈራል ፡፡አሁንም እንኳ ዙራያውን በጨለማ የታጠረ ሲኦል ውስጥ ነው የገባነው በታሪክም ባፈ ታሪክም እንዲህ አይነት ነገር አልተወራም ፡፡

እማሆይ ፡- እኔስ የምፈራው ሌላ ነው፡ ፡ዘመናይ /ዘመናይ አይኗን ትጨፍናለች / ልብሴ እንደድፍ እንዳልጠራ ጠላት ምርኮው እንዲያደርገኝ ነው፡፡ ያንን የተሸመቀ ኃጢአቴን ይዤ . . . . እንዳዘልኩት በፊቱ እንዳልቀርብ ነው ፡፡

ዘውዱ ፡- በየትኛውም ቋንቋ ይነገር አለዘዘም አልቀረም ያው ተሸከመ ነው ፍርሃት ፍርሃት ነው ፡፡ሞትም ሞት ነው ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡ ፍርሃት . . . ፍርሃት . . . ወይኔ አጥናፉ ስንቱን እንዳመጣጡ እያሳፈርኩ እንዳልመለስኩ ዛሬ አቅም ልጣ ፡፡ ዛሬ በውደቀት ልሸነፍ በባዶ ቤት ሞት ከነልጆቹ ይማርከኝ ወይኔ . . . . ወይኔ . . . አጥናፉ! በልቤ ስንት የተሸሸገ . . . ስንት የተቀበረ ሚስጥር እያለኝ በሜዳ ያለመላ ልቅር ፡፡

እማሆይ ፡- ንስሃ ግባ ያልኩህ ለዚህ መሰለኝ ፡፡ ደግሞስ ፊትህ እንዲህ የተቀያረወው ምን የከበደ ነገር አለህ ልጅ አጥናፉ

አጥናፉ ፡- ብዙ ብዙ ነገር በልቤ አለ ፡፡ሰው ሆኖ ስንት ነገረ ይኖረዋል

ዘውዱ ፡- /ወደ ሰአቱ እየሄደ / አበቃ ! አበቃ! መልአክ ሞት ወደዚህ ቤት መንገድ ጀምሯል ፡፡ ሰአቱን ተመልከቱ አምስት ደቂቃ ብቻ ነው የቀረው ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- እናንተ ባለጋሪዎቼ ሁሉ ደስ ይበላችሁ ፡፡ / ድምጻቸውን ከፍ አድርገው / ጨኸት አውጥታችሁ በእግዜሩ ደጁ ከሰሳችሁኝና ያሰባችሁት ተሳካላችሁ ፡፡ በምድር ሰርታችሁ በሰማይ ቤት መጣችሁ ደግሞሞ ደስ አይላችሁም ፡፡ እኔ አጥናፉ በፍጹም ክንዴን አልተሰራም በፍጹም አልወድቅም አልሸነፍላችሁም ....አልሸነፍም ፡፡

እማሆይ ፡- ረጋ በል ልጅ አጥናፉ መንፈስህ ተረብሿል ፡፡ ደናም አይደለህም? ትንሽ አረፉ በል

አቶ አጥናፉ ፡- እየመጣ እኮ ነው እማሆይ ሰይፉን እንደጨበጠ ሞት ወደዚህ ቤት እየገሰገሰ ነው ፡፡ እግዚአብሔር ፍርድ ይስታል እንዴ የእነሱን ጩኸት ብቻ ሰምቶ ሞትን ያከል ጠላት በውድቀት ያዘምትብኛል / እማሆይ ደግፈው ያስቀምጧቸዋል !

ዘውዱ ፡- ዘመናይ... ዘመናይ እየፀለይሽ ነው?

ዘመናይ ፡- አይደለም

ዘውዱ ፡- እና አይኖችሽ ለምን ተጨፈኑ

ዘመና ፡- አይታያችሁም . . . . እሺ አይሸታችሁም ደስ የማይል ጠረን? ወደዚህ ቤት እየቀረበ ነው ፡፡ መጥፎ ሽታ ወደዚህ ቤት ውስጥ እየገባ ነው /አይኖቿን ገልጣ አይሸታችሁም እንዴ ?

አቶ አጥናፉ ፡- /አፍንጫችሁን እያያዙ / ፐ !ፐ! እፍ . . . . ያ ግማታም ነው ፡፡

ዘውዱ ፡- እኔ ምንም አይሸተኝም ፡፡

ዘመናይ ፡- ያፍንጫህ ቀዳዳ ተደፍኗል ማለት ነው ፡፡

ዘውዱ፡- እንደማሸተት ይልና በረጅሙ ባፍንጫው ተንፍሶ /ኧረ ደህና ነው ፡፡

ዘመናይ ፡- ደህና ቢሆን ኖሮ የሚከረፋው የሞት ጠረን በሸተተህ ነበር ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- እግዚአብሔር ክፉኛ ጨከነብን፡፡ ጩኸታችንን እንዳይሰማ ጆሮዎቹን በፍርሃት መገርጣታችንን ላለማየት አይኖችሽን አሸሸ

እማሆይ ፡- ልጅ አጥናፉ....ምን ያድርግ እሱ? እኛም እንዲህ ነበር አሻፈረን ያልነው። (እጃቸውን ወደ ሰማይ ሰቅለው) እሙብርሀን ምነው ጨከንሽብን? መድኃኔአለም ምነው ልብህ ደናብን?

ዘውዱ ፡- እግዚአብሔር ዛሬ እኛን አይሰማንም

ዘመናይ ፡- ምን አልክ ?

ዘውዱ ፡- አራት ደቂቃ ብቻ ቀረ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- ወይኔ አጥናፉ ! ወይኔ ሰውየው ! አራት ደቂቃ ብቻ /ጉልበቶቻቸውን በእጆቻቸው ይመታሉ /

ዘውዱ ፡- ግን ለምን ? ስለምን እንዲህ ይሆናል ? . . . .አባዬ ! እማሆይ ስለምን ሁላችን በአንድነት እናልቃለን ?

ዘመናይ ፡- እና . . . .እና . . . ./ትጠገዋለች /

ዘውዱ ፡- እየሸሸን ያለውን እውነት እንቅረበው፡፡ የፍቅርም አይነተኛ መለኪያ ጊዜ አሁን ነው ሃቁን እንቅረበው ፡፡

እማሆይ ፡- እንዴት ልጄ ?

ዘውዱ ፡- ከመካከላችን አንዱ ሰው ራሱን መስዋእት . . . .ቤዛ አድርጎ ሌሎቻችንን ማዳን አለበት ፡፡ /በቤቱ ፀጥታ ለጥቂት ሴኮንድ ይነግሳል

ዘመናይ ፡- አዎ የረሳነው ዋና ጉዳይ ነው ፡፡ ግን ደግሞ ፈጽሞ አልረሳነውም ነበር ፡፡መልአከ ሞት እኮ ከመካከላችሁ አንድ ሰው ምረጡና እወስዳለሁ ነው ያለው ፡፡ አንድ ሰው ከውስጣችን ፈቃደኛ ከሆነ ቀሪዎቻችን እንድናለን ማለት ነው፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- /በመርበበትበት / ይሄ . . . .ይሄ እርግጥ ነው ፡፡ ይሄ . . . ይሄንንማ ሰምቻለሁ ይሄ ጨኸኝ ሊነጣጥለን አይደል እንዴ የተነሳው ይሄ . . . . .

ዘመናይ ፡- እና ታዲያ . . . .ማን . . . .ማን በፈቃድኝነት ይሄንን ይቀበላል / በፀጥታ ለሰከንዶች /

ዘውዱ ፡- በባዶ ሜዳ ከሚቸር ቁና ሙሉ የፍቅር ዲስኩር ይልቅ እውነትን አንጥራ የምትገልፀው እንዲች አይነቷ ሰዓት ናት፡፡

ዘመናይ ፡- በእርግጥ አዎ የምንዋደድ ከሆነ መረዳዳት ያለብን ዛሬ በተለይም አሁን ነው ፡፡

ዘውዱ ፡- እንደሚመስለኝ ምንም እንኳን መልአከ ሞት ለያይቶ ቢወስደንም የሚሄደው ሰው በሰማይ ቤት ትልቅ የክብር ቦታ ይኖረዋል ምክንያቱም . . .

ዘመናይ ፡- /አቋርጠው / ዘውዱ ይሄ ሁሉ ትንታኔ ምን ይረባል ሰአቱ እኮ እየበረረ ነው ፡፡ ፈቃደኛ የሚሆን ሰው እኔ ይበልና ከጭንቀት ይገላግለን ፡፡

ዘውዱ ፡- እሺ ፈቃደኛ የሚሆን የተቀደሰ ሰው ይውጣ ፡፡/ዝምታ / ፈቃደኛ የሚሆን ሰው?

እማሆይ፡- / አቋርጠውት / ይሄ ማለት እኮ ራስን በገዛ ፈቃድ እጅ ከማጥፋት አይለይም ልጆቼ እግዚአብሔር ደግሞ ራሱን ያጠፋውን ሰው ኩነኔ ቦታ ነው የሚጨምረው

ዘመናይ ፡- እሱ ራሱ እኮ ስለ ሰው ልጆች ፍቅር ብሎ ነው ራሱን ዝቅ አድርጎ ተሰቅሎ የሞተው ፡፡ ባሳለፍናቸው ጥቂት ቀናት ምሽቶች በሙሉ የነገሩኝ ይሄንን ነው አይደለም እንዴ

እማሆይ ፡- ነው ፡፡ እርግጥ ነው ፡፡/ያስነጥሳሉ /

ዘመናይ ፡- እራሱን ስለወዳጆቹ አሳልፎ ለመስጠት የሚበልጥ ፍቅር የለም ፡፡ አይደለም እንዴ አባዬ

አቶ አጥናፉ ፡- ይሆናል እንጅ ልጄ እኔ ምን አውቄ ፡፡ (ፋታ) ኧረ ልቤ ተጨነቀች . . . ኧረ ምን ይሻለኛል ነፍስና ስጋዬ በሙግት አሸበሩኝ ፡፡

ዘውዱ ፡- አበቃ ! ሰአቱ ከመሙላቱና ሁላችንም ከማለቃችን በፊት በዚህ ምድር ላይ ብዙም ብዙም ተሳትፎ የሌለው ሰው ካለ እሱ . . . . /መተያየት ብቻ ይሆናል አንዱ ወደ ወደ አንዱ /

ዘመናይ ፡- አቋርጠው አያችሁ / አባዬ እኛ ልጆች ነን ወደፊት ብዙ ማየት ይገባናል ፡፡ እ. . . /አቅማምታ / እናንተ ከኛ የተሻለ እድሜ በዚች ምድር ላይ ኖራችኋል

አቶ አጥናፉ ፡- / ተነስተው አጨንቁረው እያይዋት / እናስ . . . .እና . . . እናስ ልጄ

ዘውዱ ፡- የኔም ኃሳብ ነው ፡፡ከአንተና ከእማሆይ አንዳችሁ . . . . . .. . . . .

አቶ አጥናፉ ፡- ኧረ በስመ አብ /በጣም ይጮሃል /ኧረ በስመ አብ እኔ አሁን እኔ ብሞት አላሳዝናችሁም ልጆቼ /ፋታ / ደግሞስ ስንቱ ስራና ጉዳይ እንዳለኝ ታወቁ የለም? እናንተ ከሰው በላይ ለማድረስ ሌት ተቀን ደፋ ቀና እያልኩ አይደለም

ዘውዱ ፡- እማሆይስ . . .አንደኛ የሚች እናታችን እህት ነዎት ሁለተኛ አለምን ትተው ለነፍስዎ ያደሩ ነዎት ሦስተኛ

እማሆይ ፡- /ትክዝ ብለው / እሄ ልጅ!.... ልጄ እኔማ ስንት በደል ስንት ኃጢአት በጫንቃዬ ተሸክሜያለሁ መሰለህ ሌላ ፈልግ ልጄ ገና ንስሀ ሳልገባ? ስንት ነገር ይቀረኛል

ዘመናይ ፡- ሌላ.. ሌላ ማን አለ እኔ ነን ፡፡ እኔ ለሞት አልተፈጠርኩም . . . ማለቴ ጊዜዬ ገና ነው ፡፡

እማሆይ ፡- ታዲያ እኔ ለገዳሙ ስራ ታዥገዤ ወደዚህ እንደመጣሁ ታወቁ የለም እናንተ አዘገያችሁኝ እንጅ ስንት መልአክት እንዳዘልኩ ታውቁ የለም ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- ቢሆንም ከኔ ይሻላሉ እማሆይ እርሶ ያለምን ጣጣ ጨርሰዋል ፡፡ እኔ የሙት ልጆች እያሳደኩ ነው ፡፡ በሜዳ ትቻቸው ብሄድ ያለእናት ያለ አባት መቅረታቸው ነው ፡፡

እማሆይ ፡- ቢሆንም ! ቢሆንም ! አቶ አጥናፉ በድፍረት ልሄድ የሚያስችኝ ምግባር በኔ ውስጥ የለም ፡፡ ለጉዞ እኮ ስንቅ ያስፈልጋል ፤መዝገቤ በኃጢአት የጠቆረ ነውና እስኪፋቅልኝ ድረስ ጥቂት ጊዜ ራሴን በፊቱ ማዋረድ ይኖርብበኛል ፡፡

ዘውዱ ፡- ያለመታደል ነው!!!! ሁሉም ነገር ከንቱ ሆነ አባዬ እኮ ልታድነን ይገባ ነበር ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- ልጄ ከሁለት መቶ ሺህ ብር በላይ ወጪ ተዝረክርኮ ይገኛል ፡፡ የነገው ሰኞ ደግሞ በህግ አስፈርጄ የምቀበለው ስልሳ ሺህ ብር አለ፡፡ እኔ ከሌለሁ ሁሉም ነገር መና ቀረ፡፡

ዘመናይ ፡- ገንዘቡም አሁንም መና ከመቅረት አልዳነም እንኳን ገንዘቡ እኛ ልናልፍ ነው ከደቂዎች ቡኃላ በቤታችን ላይ እቶን ይወርዳል ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- የሶደምና የገሞራ ቅጣት በእኛ ላይ መጣ ፡፡ ነነዌን የማርክ አምላክ እባክህ ቁጣህን መልሰው ፡፡ /እየተርበተበተ / እንዴ ! እንዴ ! . . . ዘውዱ እንዴ ኪሳቸውን ይደባብሳሉ

ዘውዱ ፡- ምነው አባዬ ከጭንቀት ልታድነን ልትገላግለን ነው /ጉጉት ይጠጋል /

አቶ አጥናፉ ፡- የለም ! የለም ልጄ ! ሚስጢሩ ተሸሽጎ መቅረት የለበትም ፡፡

ዘውዱ ፡- የምን ሚስጢር

አቶ አጥናፉ ፡- ሞት ሳይቀድመኝ መቅደም አለብኝ ፡፡ ባላጋሪዎቼን ሁሉ ብሞትም አሸንፌ ነው የምሞተው ፡፡/እንደ አዞረው ሰው ያደርጋቸዋል ራሳቸውን ይይዛሉ ፡፡/

ዘመናይ ፡- ምነው ምንድ ነው አባዬ

አቶ አጥናፉ ፡- ኑዛዜ ኑዛዜ አለኝ ያንን ብስብስ ሰይጣን ልቅደመው ፡፡/ በፍጥነት መኝታ ቤታቸው ይገባሉ ዘመናይ ትከተላቸዋለች ፡፡/

እማሆይ ፡- አዬ ቤዛይታለም የአባትነት አንጀት አስገድዶት ለመሞት ቀረጠ ማለት ነው ንስሃ እንኳን በወጉ ሳይገባ ሊሞት ቀረጠ

ዘውዱ ፡- ታዲያ ኑዛዜው ምንድ ነው (ሰዓቱን አይቶ) በፍጹም መቀደም የለብንም

አቶ አጥናፉ ፡- /ወረቀትና እስክርቢቶ ይዘው ይወጣሉ) ሰአቱ አለቀ ፡፡ ሳልናዘዝ ሰዓቱ አለቀ

ዘውዱ ፡- ምን ብለህ ነው የምትናዘዘው

አቶ አጥናፉ ፡- ልጆች! (ፋታ) ከውጪ . . . .ምናልባት ሁላችንም ከሞትን.... ከውጪ የሚወለዱ ሁለት ልጆች አሉኝ ፡፡

ዘውዱ /ዘመናይ/ ፡- (በአንድነትና ባለማመን ስሜት) ምን??!!

እማሆይ ፡- ሰዓሊነ ቅድስት ! (ሁሉም አፍጠው ተጠጓቸው)

እቶ አጥናፉ ፡- እኔ ከሞትኩ ገንዘቤን ሁሉ ተከራክረው ማስመለስ አለባቸው ፡፡ ለሰው መሳቂያ ሆኜ አልሞትም! በሜዳ የተዘራ ብሬን . . . . .

ዘውዱ ፡- /በጥላቻና በመገረም ስሜት ተውጦ / ምንድ ነው የምታወራው- ሸሽገህ ያኖርኳቸው ልጆች አሉ? / በጣም እየተንከተከረ ይስቃል/

ዘመናይ፡- /እየተመናጨቀች/ እሺ ለምን ትነግረናለህ አትንገረን አትንገረን

ዘውዱ ፡- እኒያ ልጆችህ አባትነትህን ማመስገን አለባቸው /ፋታ/ እንደዚህ አይነት ጎሊናን የሚከብዱና የሚቧጥጡ ነገሮች አፍጠው ሲመጡ የሰው ልጅ ምን ማድረግ አለበት

አቶ አጥናፉ ፡- እባክህ መፈላፈስን ተወወና ወረቀቱንና መጻፊያውን ተቀበለኝና ቶሎ ጻፍልኝ (የተዘረጋ እጃቸውን እንዲያውም) ፍርዱን ሁሉ ወደኔ አታዙረው እንጂ ዘውዱ ተዛዝበናል እኮ አልድናችሁም አልከን?

ዘውዱ ፡- (ጥሏቸው እየሄደና ወረቀቱን እየሰጣቸው) እድሜያችሁን እንደ ሾርባ ጨልጣችሁ የጠጣችሁት ስትፈሩ - እኔ ልሞት?! እኔም ላለመሞት አንድሺ ምክንያት አለኝ፡፡ አምሳያዬን በማህፀኗ የያዘች ፍቅረኛ አለችኝ ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- (በመገረም) /ቱ . . . . . . .ቱ . . . . . . .

ዘመናይ ፡- እኔም እናንተ የፈራችሁትን ሞት የሚሸከም ጫንቃ የለኝም፡፡ ቢልልኝ ኖሮ አስራ ሁለት ዓመት በሙሉ የደከምኩበት ትምህርት ውጤት ስለመጣልኝ ዩኒቨርስቲ ገብቼ ወይ ዶክተር አለበለዚያም ኢንጅነር እሆን ነበር

አቶ አጥናፉ ፡- ኧረ እባክህ አንተ ጉደኛው የሆነው ሆኖ ና ጻፍ ፡፡

ዘውዱ ፡- ወረቀቱ ከእንግዲህ አያገለግልም ልጆችህም ለዘላለም ሲረግሙህ ይኖራሉ ፡፡ አንድ ሀሳብ ሳትገልጽ ሙብረቅ በዚህ ቤት ላይ ይወድቃል። ኡ...ኡ..! (ወፈፍ እንደሚያደርገው ሰው እየጮኸ) አበቃ ! ሰዓት ሞላ ! የሚያስጠላ በሽታ ለኔም አፍንጫ ደረሰ ፡፡ ሞት . . ሞት . .ደም . . .ደም . . .እሳት . . . እሳት . . .የሚሸተው ነገር በቤቱ ተረጭቷል (ማታ ከነበረበት ወንበር ላይ ይቀመጣል)

አቶ አጥናፉ ፡- ተወው ! ተወው ! ንፈግ ፡፡ አወላግጄም ቢሆን እደፈዋለሁ (በመጀሪያ ከነበሩበት ጠረጴዛው ሆነው መጻፍ ይጀምራሉ)

ዘመናይ ፡- አባዬ ጡርዬ ብትኖር . . . .እማዬ ብትኖር ምን ትልህ ነበር? (አይኖቿን ጨፍና እርሷን ይዛ ትቆማለች)

ዘውዱ፡- አንድ ደቂቃ ብቻ ቀረ!

እማሆይ፡- /ይንበረከካሉ/ ማረን ፤ አቤቱ ማረን . . .ማረን . . . ማረኝ አቤቱ . . .ማረኝ

ዘመናይ ፡- ስለሁላችን ቤዛ የሚሆን አንድ ሰው ጠፋ ? እናም ሁላችንም ልንሞት ነው ? እማዬ ብትናገር ኖሮ አትጨክንም ነበር ፡፡

አቶ አጥናፉ ፡- እኔም አባትሽ ነኝ እኮ ልጅ ?

ዘውዱ ፡- (ምርር ባለ የትዝብት ድምጽ) ግን ጨከንክብን።

አቶ አጥናፉ ፡- /ቀና ብለው/ መጨከን አይደለም ልጆቼ ማንም ከሞት ጋር መተናነቅ አይችልም ሰዓቱን አይተው በፍጥነት ይጽፋሉ

ዘመናይ ፡- አበቃ ሁሉም ነገር ሊፈጸም ነው ፡፡ እሳት ከሰማይ እየተቀጣጠለ ነው /ትንበረከካለች / እናታችን ትታየሃለች ዘውዱ ? እማዬ አየሃት

ዘውዱ ፡- አትታየኝም . . . . .አትታየኝም

እማሆይ ፡- /ድምጻቸው ድካም ባለ / እግዚአብሔር ሆይ ሀጢአቴን ሁሉ ይቅር በል ባሌን በቅናት ተነሳስቼ ገድየዋለሁ፡፡ (ሁሉም በድንጋጤ እማሆይን ያያሉ-ወዲያው እርስ በርሳቸው ይተያያሉ) መሳሳቴን አውቄ ያንተኑ ደጅ እጠናለሁ ሃጢያቴን ይቅር እንድትለኝ ተሰድጄ ውሎዬና አዳሬ ከድር አራዊት ጋር አድርጊያለሁኝ ማረኝ ማረኝ (ሁሉም ከያሉበት ስርቻ ይወሽቃሉ። ሰዓቱ ሲጮህ በፍርሀት ፍጹም ፀጥታ ይነግሳል ሁሉም በፍርሀት ተጨማደው አንዳች ሀይል አናታቸውን እስኪጫናቸው ይጠብቃሉ እናም ሙሉ ደቂቃ ያልፋል፡፡ በመጀመሪያም አቶ አጥናፉ አይናቸውን ገልጠው ቤቱን ይቃኛሉ፡፡ ከዚያም ዘመናይ ቀጥሎ እማሆይ ሀና አይናቸውን ገልጸው ከተንበረከኩበት ይነሳሉ፡፡ ጥቂት ጊዜ ፀጥታ እርስ በርሳቸው ይተያያሉ)

አቶ አጥናፉ፡- ቀጠሮውን ዘንግቶታል

ዘመናይ ፡- እማሆይ . . . . እባዬ . . . .ዘውዱ የለም ወስዶት ነው

አቶ አጥናፉ ፡- አዬ ጉድ ልጄ አላፊ አብዝቶ ነበር፡፡



ወስብሐት ለእግዚአብሔር